# ወንድ መሆን ካማረህ (ግጥም ለወጣቱ)

## አንተነህ (ከቶሮንቶ)

አንድ ሕይወት አለህ፣ አንድ ሞት አላቸው፣
ገዝግዘው ሲገድሉህ፣ ምነው ዝም አልካቸው?!

ወጣቷ እህቴ፣ ጀግንነት ያባትሽ፣
ትዳር የተፈጥሮ፣ መሻት መፈለግሽ፣
ወንድ ሁሉ ወንድ አይደል፣ ምክር ልለግስሽ፣
ቃጭል ቢኖረውም፣ አንቺው ትበልጫለሽ፣
ጀግናውን ከፈለግሽ፣ ኢሕአፓን ልዳርሽ።

ፍርሃት ከወረረህ፣ ቀሚሱን ልበሰው፣
ነጠላውን ደርብ፣ ታኮውን ተጫማው፣
ሊፒስቲክ ተቀባ፣ ኩሉንም ተኳለው፣
ቁጭ ብለህም ሽና፣ መቆምህን ተወው፣
ፈጥኖህ እንዲወስድህም፣ አምላክን ለምነው፣
በድንህ ቢንቀሳቀስ፣ ምንም አትጠቅመው።

እያወክ መተኛት፣ ዝም ብለህ መጋደም፣
ሀገርህ ስትሸጥ፣ ሃይማኖት ሲከለስ፣ ገዳማት ሲወድም፣
ህግ በሌለበት፣ ሀብት ለማፍራት መድከም፣
የጨው ገደል ሲናድ፣ ለትርፍ እሽቅድድም፣
ምንም አላዝንልህ፣ አብረሃቸው ውደም!

መነሣት ከፈለግህ፣ ታሪክህን ማደስ፣
ይጠበቅብሃል፣ ብድርን መመለስ፣
ባንዳውንም ማክሰም፣ ወያኔን መደቆስ፣
ሃገርህን ማዳን፣ ክብርህን ማስመለስ፣
ሕዝብህን መታደግ፣ ጠላት ማተራመስ፣
በያም፣ በፍስኩ፣ ወያኔን ብላና፣ "ቼ!' ብለህ ተቀደስ።

ወንድነትህን መልስ፣ ወንድ መሆን ካማረህ፣
ከበድን መላቀቅ፣ ትንሣኤንም ከሻህ፣
ኢሕአፓን አማክረው፣ ጀግናውን ጠይቀው፣ ምስጢሩን ይንገርህ።

ሃገርህን ውደድ፣ ሕዝብህን አስቀድም፣ መብትህንም ንጠቅ፣
ቅንጣቢ አይመርህ፣  ጠላትህንም ለይ፣ ወዳጅህን እወቅ፣
ባንዶችን ማርከሻ፣ ለወያኔዎች ጠንቅ፣
ኢወክንድ ጠበሉ፣ በየቦታው ይፍለቅ!
አንተም ተጠመቀው፣ ልክፍትህም ይልቀቅ!

ይልቀቅ ፍርሃትህ፣ ወንድ ሁን እንደገና፣
ጠበሉን ተጋተው፣ ለመፍትሄ ፍውስና፣
ቅዳሴ ዜማውም፣ ኢሕአፓ ነውና!